# መልዕክታችን ከልብ ነው!

**አባ መላኩ 06-12-18**

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ  አባይን በተመለከተ ለግብጻዊያን የማይናወጠውን የህዝባቸውንና የመንግስታቸውን አቋም አስረግጠው ነግረዋቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትራችን "እኛ ኢትዮጵያዊያን ወንድምነትንና መልካም ጉርብትና የምናውቅ፤ እግዚአብሔርን የምንፈራ ስለሆንን ወንድም ህዝብ የሆነውን የግብጽ ህዝብ በፍጹም፣ በፍጹም የመጉዳት ሃሳብም ፍላጎትም የለንም" ብለዋል። ታላቁ የኢትዮጵያ  የህዳሴ ግድብ  ማንንም ሳይጎዳ  ኢትዮጵያዊያንን መጥቀም የሚያስችል ፕሮጀክት ነው።  ይህ ፕሮጀክት ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ባሻገር ለእኛ ኢትዮጵያዊያን  ሌላም ሌላም  ነገር እንደሆነ  ልትረዱልን ይገባል። ይህ ፕሮጀክት የለውጥ፣ የዕድገት፣ የአንድነት፣ የአብሮነት ማሳያ በመሆኑ ማንንም ሳይጎዳ እኛን የሚጠቅም ነው። አንዳንዶች  ታላቁ  የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ  ከአድዋ ጦርነት በመቀጠል  ኢትዮጵያዊያኖችን በአንድ ጥላ ስር ማሰባሰብ የቻለ ፕሮጀክት እንደሆነ በአደባባይ ሲመሰክሩ ይደመጣሉ። ከዚህም ባሻገር ለአገራዊ መግባባትና ለገጽታ ግንበታ ስራችን ያለው  ሚናም  በቀላሉ  የሚታይ አይደለም።

እውነታ እስከ ዛሬ በአገራችን በርካታ ስራዎች እይተከናወኑ ቢሆንም እንደህዳሴው ግድብ የህብረተሰቡን ቀልብ የገዛ ህዝቡን በአንድ ጥላ ስር ያሰባሰበ  ፕሮጀክት  አልታየም። እዚህ ፕሮጀክት ላይ ከአዋቂ እስከ ህጻን፣ ከምሁር እስከ አልተማረው፣ ከሃይማኖት መሪው እስከ ምዕመኑ፣ አገር ቤት ከሚኖረው እስከ ዳያስፖራ ወዘተ አሻራውን በዚህ ፕሮጀክት ላይ ያላሳረፈ አገር ወዳድ ዜጋ የለም። አሁን ላይ ይህ ፕሮጀክት ወደ 66 በመቶ ማድረስ ተችሏል፤ አሁንም ለፕሮጀክቱ እውን መሆን የህዝብ ድጋፍ መጠናከር ያለበት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም  እየሰማንና እየተመለከትን ካለነው ነገር  አዲሱ አመራር በተለይ የውጭ ምንዛሬን በተመለከተ ባዶ ካዝና  እንደተረከቡ ነው። በመሆኑም ህብረተሰቡ ለዚህ ፕሮጀክት እስካሁን  እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል  ይኖርበታል።

ባለፉት ዓመታት አንዳንድ የውጭ ሃይሎች የህዳሴውን ግድብ ለማደናቀፍ ያመቸናል ያሉትን መንገድ ሁሉ ለመተግበር ወደኋላ  እንደማይሉ አንዳንድ ማሳያዎች እንደነበሩ የአደባባይ ሚስጢር ነው። ዛሬ ላይ ማንም የውጭ ሃይል በውስጥ ጉዳያችን ይገባል ብለን እንዳንሰጋ ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ ግንቡን

ደርምሰውታል። አዲሱ የአገራችን አመራሮች እርቅ የወረደባት አዲሲቷን ኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ናቸው። ይህ አመራር ምስጋና ይግባውና በኢትዮጵያ የቁርሾ ፖለቲካ አካሄድን እንዲያበቃ ጠንክሮ በመስራት ላይ ነው። የዶ/ር አብይ መንግስት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ ሳቢያ አኩርፎ ወደ ውጭ የሚሄድበትን ሁኔታ እንዳይኖር እንዲሁም በተለያየ መንገድ ተገፍቶ በውጭ ያለ ሃይል ሁሉ ወደ አገር ቤት ተመልሶ ሰላማዊ ትግሉን እንዲቀላቀሉ የፖለቲካ ምህዳሩን አስፍተውታል።

ዶ/ር አብይ በኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት በርካታ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ናቸው። ይህን አይነት አካሄድ አገራዊ አንድነትን ከማጠናከሩ ባሻገር የውጭ ሃይሎች ጣልቃ የሚገቡበትን መንገድ ይዘጋል። የግብፃዊያን ፖለቲከኞች፣ ምሁራንና ሚዲያም አዲስቷን ኢትዮጵያ እየሰራች ያለውን ሁኔታ ሊገነዘቡትና እውነታውን አውቀው አካሄዳቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል ባይ ነኝ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ ለግብጻዊያን የሰጧቸው ቃል የማይታጠፍ መሆኑን የግብጽ ሃይሎች ተገንዝበው ስለህዳሴው ግድብ ያላቸውን አተያይ ሊያስተካክሉ ይገባል። የግብጽ ሃይሎች ኢትዮጵያን ይመለከቱበት የነበረው የቀድሞው ያረጀና ያፈጀ መነጽራቸውን በመቀየር ትክክለኛ ምስላችንን የሚያሳየውን አዲስ መነጽር ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት ያለባት፤ ሚሊዮኖች ከድህነት ጠለል በታች የሚኖሩባት አገር መሆኗን ግብጻዊያን ተረድተው ልማትና ዕድገት እንደሚያስፈልጋት አምነው መቀበል ይኖርባቸዋል። የዓባይ ቀጣይ ህይወት ሊረጋገጥ የሚችለው በላይኞቹ የተፋሰስ አገራት ዘላቂ የአካባቢ ልማት ስራ ሲከናወን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ እውን የሚሆነው የላይኞቹ የተፋሰስ አገራት ከወንዙ ፍትሃዊ ተጠቃሚ ሲሆኑ ብቻ ነው። አሁን ላይ ኢትዮጵያ ሰፊ የተፋሰስ ልማት ስራ በማከናወን ላይ ስትሆን ይህ ደግሞ የወንዙን ቀጣይ ህይወት የሚያረጋግጥ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ኢትዮጵያ የግብጽን ህዝብ ለመጉዳት የምታደርገው አንድም ነገር እንደሌለ አስረግጠው ነግረዋቸዋል። ግብጻዊያን ይህን ዕውነታ ተቀበሉ፤ በጠቅላይ ሚኒስትራችን በኩል ያደረሷችሁን መልዕክት ከልብና እውነታ ነው። ኢትዮጵያ መቼም ቢሆን ቃሏን አጥፋ አታውቅም።

አባይን በትብብር ማልማት ቢቻል ለሁሉም የሚተርፍ የጋራ ሃብት ነው። ኢትዮጵያ ከሱዳንና ከግብጽ የተሻለ ለሃይል ማመንጫነት የሚያመች የተፈጥሮ አቀማመጥ ያላት አገር ስትሆን ግብጽና ሱዳን ደግሞ ከኢትዮጵያ የተሻለ ለመስኖ የሚውል መሬት እንዳላቸው ይታወቃል። የሃይል ማመንጫ ደግሞ ውሃን

የሚያባክን ባለመሆኑ በታችኞቹ የተፋሰስ አገራት ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ይህ ፕሮጀክት ግብጻዊያን የውሃ ድርሻቸው ሳይቀንስ እንጠማለን እንራባለን ብለው ሳይሰጉ እኛ ኢትዮጵያዊያን ልንጠቀም የሚያስችለን ነው። ይህንንም ጠቅላይ ሚኒስትራችን አረጋግጠውላቸዋል።

አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞች፣ ምሁራንና ሚዲያዎች ወቅታዊውን የኢትዮጵያ ሁኔታ ፈጽመው የተገነዘቧት አይመስለኝም። አሁን ላይ ኢትዮጵያ አዳዲስ አመራሮች በአዳዲስ አስተሳሰብ ታጀባ በለውጥ ጎዳና ላይ ነች። በመሆኑም አዲሱ አመራር ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ያለው በመሆኑ ማንኛውም አካል ጣለቃ ሊገባባት አይችልም። እንደእኔ እንደእኔ ከእንግዲህ አገራችን በውስጥ ጉዳያ የውጭ ሃይች ጣልቃ ሊገቡበት የሚችሉበትን መንገድ ዶ/ር አብይ ዘግተውታል ብዬ አምናለሁ።

ታሪክ እንደሚነግረን ኢትዮጵያ በየትኛውም አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብታ አታውቅም። ይህ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችንም ውጤታማ እንድንሆን አድርጎናል። የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ “ፍትሃዊነት” የኢትዮጵያ የትላንት፣ የዛሬና የነገም አቋም ነው። አገራችን የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ ከወንዙ ማግኘት የሚገባትን እኩል ተጠቃሚነት የሚለውን ዓለም ዓቀፍ መርህ ይተግበር የሚል አቋም አልተከተለችም። ይልቁንም ነበራዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት “ፍትሃዊነትን” መርጣለች። አባይ በትብብር የሚለማ ከሆነ የተፋሰሱ አገራትን በሙሉ በጥቅም ሊያስተሳስር የሚችል ትልቅ ሃብት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ እንደገለጹት ይህ ሃብት ለሁሉም የሚበቃ በመሆኑ የግብጽም ሆኑ የኢትዮጵያ ሚዲያዎች ለሁለቱ አገራት ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት መስራት ይኖርባቸዋል። ባለፉት በርካታ ዓመታት በሁለቱ አገራት መካከል ውጥረት እንዲፈጠር ሚዲያዎች ከፍተኛ ሚና ነበራቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይና ፕሬዚዳንት አል ሲሲ በፕሬስ መግለጫው ላይ እንደተናገሩት የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ስትራቴጂያዊ አጋርነት ያለውና የሁለቱንም ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን ከስምምነት ደርሰዋል። የሁለቱን ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነተ ለማሳደግ ከሚያግዙት ነገሮች መካከል ደግሞ በኢትዮጵያ የግብጻውያን ኢንቨስተሮችን ቁጥር ማሳደግ፤ እንዲሁም በግብጽ፣ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ነው። ዶ/ር አብይ ለግብጻዊያን አስረግጠው እንዳሉት “እኛ ኢትዮጵያዊያን ወንድምነትንና መልካም ጉርብትና የምናውቅ፤ እግዚአብሔርን የምንፈራ ስለሆንን ወንድም ህዝብ የሆነውን የግብጽ ህዝብ በፍጹም፣ በፍጹም የመጉዳት ሃሳብም ፍላጎትም የለንም” ብለዋል። ይህ ለግብጻዊያን በተደጋጋሚ የተገለጸላቸው የኢትዮጵያ ጽኑ አቋም ነው። ግብጻዊያን የአስዋን ግድብ ሁለመናቸው

አድርገው እንደሚመለከቱት ለእኛ ኢትዮጵያዊያንም ታላቁ የህዳሴ ግድባችን ከሃይል ማመንጫ ግድብነት ባሻገረ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል። በመሆኑም ለእነርሱም ሆነ ለእኛ የሚበጀን ተቀራርቦና ተማምኖ መስራት እንጂ ፍጥጫ አይደለም።

ውጥረት ለማንም እንደማይበጅ የኢትዮጵያ መንግስት በተደጋጋሚ ሲገልጸው ቆይቷል። ከማንኛውም አካል ጋር ተባብሮና ተቀራርቦ ለመስራት አዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት ዝግጁ መሆኑን በተግባር እያሳየ ነው። ዛሬ ላይ ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ ካይሮ ድረስ ሄደው ግብጻዊያንን እንዲረጋጉ ማድረጋቸው ይበል የሚያሰኝ የዲፕሎማሲ ስራ ነው። ዶ/ር አብይ ምስጋና ይግባቸውና በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭም ያሉ ኢትዮጵያዊያን የቁርሾና የመጠራጠር ፖለቲካ አካሄዶች እንዳይከተሉ ሁኔታዎችን ቀይረዋቸዋል። ግብፃዊያን ፖለቲከኞች፣ ምሁራንና ሚዲያዎች አዲስቷን ኢትዮጵያ እየሰራች ያለውን ሁኔታ ተገንዝባችሁ እናንተም ይህን ፈር ብትከተሉ መልካም ነው ባይ ነኝ።

ለግብጽም ሆነ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም የሚበጀው ተቀራርቦ፣ ተሳስቦና ተደጋግፎ መስራት እንጂ በጥርጣሬ መተያየትና መፈራረጅ አይደለም። ከአዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት አካሄድ መረዳት እንደሚቻለው ከሁሉም አገራት ጋር ተቀራርቦና ተማምኖ ለመስራት ቆርጦ መነሳቱን ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያው አስቸጋሪ ለሚባለው ለኤርትራ መንግስት ሳይቀር ተቀራርቦ ለመስራት የሰላም ጥሪ ማቅረቡ ነው። ይህ አይነት አካሄድ ይበል የሚያሰኝ፤ በሌላኛውም ወገን ያለው አካል ይህን አካሄድ ቢከተለው መልካም ነው።